ሚያዚያ 16 ቀን 2000 ዓ/ም

ለተከበራችሁ የዳላስ ፎርትዎርዝ ኢትዮጵያውያን ነዋሪዎች

<u>ጉዳዩ፡ እድር ለማቋቋም ስለቀረበው ደንብ</u>

በመጀመሪያ የማክበር ሰላምታችንን እናቀርባለን።

## 1. ችግሩ

1.1 እንደሚታወቀው ሰው ሆኖ በመጨረሻው ሞት የማይቀር በመሆኑ በዳላስ ፎርትዎርዝ ነዋሪዎችም መሀል ይህ ሁኔታ በልዩ ልዩ ምክንያቶች እየተከሰተ ነው። እስካሁንም ድረስ እንደታየው በማሕበራችን ሞት ሲያጋጥም የሚከናወነው የአሸኛኘት ዘዴ ለሟቹ ዘመዶች እና ወላጆች የሚያሸማቅቅ ለቀብሩ ወጪ ገንዘብ በመለመን ሲሆን ቆይቷል።

1.2 ሌላው ከባድ ችግር በማሕበራችን አብዛኞቻችን ሞት አይቀሬ መሆኑን ተገንዝበን የሕይወት ኢንሹራንስ እና ሕጋዊ ኑዛዜ ስለማናዘጋጅ ጥረን ግረን ያካበትነውን እንኳ ቀልጦ ከመቅረቱ በላይ ቀሪዎቹ ቤተሰቦቻችን ችግር ላይ ይወድቃሉ።

## 2. መፍትሔው

2.1 ከላይ ከተጠቀሰው ችግር ለመላቀቅ እና በኢትዮጵያዊ ባሕላችን ተገቢ የሆነ መፍትሔ ለመስጠት ሁሉንም የሚያሳትፍ እድር ማቋቋም አስፈላጊ መሆኑን አምነንበታል። በተጨማሪም በአሜሪካ ሕግ እና የኑሮ ዘዴ መሰረት የእድሩ አባላት ስለ ሕይወት ኢንሹራንስና ስለ ኑዛዜ ቀደም ብሎ ማዘጋጀት አስፈላጊነት ጠለቅ ያለ ግንዛቤ እንዲያገኙ ማድረግ ለራሳቸውም ለቤተሰባቸውም እንደሚጠቅም አምነንበታል።

## 3. ረቂቅ የእድር ደንቡ ዝግጅት

3.1 እድር ማቋቋም አማራጭ የሌለው መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ ተገቢ የሆነ ረቂቅ ደንብ ማዘጋጀቱ አስፈላጊ ስለሆነ አንድ ኮሚቴ ተቋቁሞ ጉዳዩን ለብዙ ወራት ከፍ ባለ ጥንቃቄ ሲያጠና ከቆየ በኋላ ሥራውን አጠናቆ ረቂቁን ለዳላስ የኢትዮጵያውያን መረዳጃ ማህበር ቦርድ አቀረበ።

3.2 የማሕበሩ ቦርድም በበኩሉ ረቂቁን በጥሞና ተመልክቶ ከአርቃቂው ኮሚቴ ጋር በቅርብ በመመካከር ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚገኘውን የተሻሻለ ረቂቅ ለሕብረተሰቡ አቅርቧል።

3.3 አሁን የሚያስፈልገው ማሕበረሰቡ ረቂቁን በዝርዝር ተመልክቶ የሚስተካከለውን አስተካክሎ እንዲያጸድቀው ነው።

## 4. የረቂቅ ደንቡ ገጽታዎች

4.1 ረቂቅ ደንቡ በግልጽ እንደሚያሳየው፡ እድሩ የሚቋቋመው ከመረዳጃ ማሕበሩ አካሎች አንዱ ሆኖ ተግባሩን እንዲያከናውን ነው።

4.2 በረቂቅ ደንቡ መሠረት የእድሩ አወቃቀር የበላይ ወሳኝ አካል የእድሩ ተሳታፊዎች ጠቅላላ ጉባኤ ሲሆን ከዚያ በታች የማሕበሩ ቦርድ፤ ከቦርዱ በታች የእድሩ የበላይ ተቆጣጣሪ ኮሚቴ፤ ከዚያም በታች የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ሲሆኑ በተጨማሪ ቦርዱን የሚያግዙ አስመራጭ ኮሚቴ እና የሂሳብ መርማሪና የህዝብ ግንኙነት ዘርፍ ተካትተዋል።

4.3 የእድሩ ደንብ የተዘጋጀው በአሠራሩ ግልጽነት ጥብቅ ቁጥጥር እንዲኖረው ሆኖ የእድሩን ተሳታፊዎች ሙሉ እምነት እንዲያገኝ በማመቻቸት ነው።

4.4 የማሕበሩ ቦርድም ሀላፊነቱን በብቃት እንዲያከናውን ለማድረግ ጥቂት አባሎቹ በእድሩ ተቆጣጣሪ ኮሚቴ እና በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተግባሮች እንዲሳተፉ ተደርጓል።

4.5 በደንቡ መሠረት በየወሩ፤ በየሦስት ወሩ እና በየአመቱ የሚቀርቡ ሪፓርቶች ስለሚኖሩ፡ የእድሩን የንብረት እና የሂሳብ ሁኔታ በየጊዜው በጥራት መመልከት ይቻላል ማለት ነው።

## 5. ልዩ ትኩረት የሚገባቸው ጉዳዮች

ረቂቅ ደንቡን የሚመለከተው ይህ ጉባኤ በጥንቃቄ አንቀጽ በአንቀጽ እንደሚመረምረው ብንገነዘብም ልዩ ትኩረት ይገባቸዋል ብለን የምንገምታቸውን ነጥቦች ከዚህ በታች እናቀርባለን።

5.1 ረቂቅ ደንቡ ውስጥ ከተጠቀሱት አንዱ፤ የእድሩ አባል በሞት ሲያልፍ ለቤተሰቡ $10, 000 (አስር ሺህ) ዶላር መከፈል ያለበት መሆኑን ነው። ይህንን ነጥብ ከአርቃቂ ኮሚቴዎች አብዛኞቹ ያመኑበት ቢሆንም ሌላም አናሳ አስተያየት ነበር። ይህም ወደፊት የሚመረጠው የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ጉዳዩን በጥንቃቄ አጥንቶ ሊከፈል የሚገባውን የገንዘብ መጠን አቅርቦ በእድሩ የተቆጣጣሪ ኮሚቴ እና የማህበሩ ቦርድ ተመርምሮ ለእድሩ ተሳታፊዎች ጉባኤ አቅርቦ ይወሰን የሚል ነው።

5.2 እድሩ ከተቋቋመ በኋላ ወዲያውኑ ለቀብር የሚከፈለው ገንዘብ ስለማይኖረው እስከ ሦስት ወር ድረስ ክፍያ እንደማይኖር እና በዚህም ምክንያት ወደፊት በእድሩ አባልነት የሚመዘገቡ ሰዎች ሁሉ ለመጀመሪያው ሶስት ወር የመከፈል መብት እንደማይኖራቸው ረቂቅ ደንቡ ያዛል።

5.3 እድሩ የመረዳጃ ማሕበሩ አካል በመሆኑ የሚያገኘው ጥቅም፤ በማህበሩ የቀረጥ ነጻ መብት ከመጠቀሙ በላይ የማሕበሩን ሙሉ ድጋፍ ስለሚያገኝ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲጠናከር ያስችለዋል። በማሕበሩ በኩል ደግሞ የእድሩ አገልግሎት ለአባሎቹ አስፈላጊ እና ጠቃሚ ስለሚሆን አርኪ ውጤት ሊያስገኝለት ከመቻሉ በላይ፤ ከአጉል የፉክክር ጠንቅ እንደሚያድነው የታወቀ ነው።

5.4 የእድሩ አባሎች መፈጸም ያለባቸው ክፍያ መጠነኛ እንዲሆን ከመደረጉ በላይ ለእድሩ ተሳታፊነት ለማበረታታት ለማሕበሩ አባልነት ከሚከፍሉት ቅናሽ እንዲያገኙ ተደርጓል።

## 6. መደምደሚያ

ጉባዔው ከላይ በተጠቀሱት ጉዳዮችና በረቂቁ ደንብ የተካተቱትን ሀሳቦች በጥንቃቄ ተመልክቶ ግልጽ ውሳኔ በማሳለፍ የእድሩ ተግባር በተቻለ ፍጥነት እንዲጀምር በትሕትና እናሳስባለን።

ተፈራወርቅ አሰፋ
የኢትዮጵያውያን መረዳጃ ማሕበር ቦርድ
ሊቀመንበር